# ለአማራ መጥፋት የአማራ ድርሻ

**Melek Hara** **(Thurs September 23, 2015)** ·

**https://www.facebook.com/permalink.php?story_fbid=174306686238775&id=100009783333517**

=================

አማራ ዛሬ ለተጋረጠበት የጥፋት እና የሰቆቃ ህይወት እስካሁን ድረስ ውጫዊ ምክንያቶች ላይ አተኩረን ስንጽፍ ቆይተናል፡፡ አለፍ ገደም በሆነ ሁኔታ ነካክተነው ይሆናል እንጅ ዋናውን ችግር አልገለጥነውም፡፡ አማራን አማራ እንጅ ማንም አቅም አግኝቶ ሊያሸንፈው አይችልም ብለን እንንደርደር፡፡ ከቅርቡ የአድዋ ጦርነት እንጀምር፡፡ በአድዋ ጦርነት ጀግኖች ወድቀዋል፡፡ በዛ ጦርነት በጀግኖች ቁጥር ላይ ለውጥ እንደሚመጣ መገመት አይከብድም፡፡ የጀግኖች ቁጥር ማነስ ተከታዩን ትውልድ በስፋት ጀግንነት አላብሶ ለማሳደግ የነበረውን ሚና ቀንሶታል፡፡ መጠነኛም ቢሆን ባህልን፤ ጀግንነትን እና ታሪክን አውራሽ የሆኑ ትውልዶች ያላቸውን ጀግንነትና እውቀት ለቀጣዩ ትውልድ ሙሉ በሙሉ ሳያስተላልፉ ቀርተዋል፡፡ ይህም አሉታዊ ማህበራዊ ተጽእኖ አምጥቷል ብሎ ለመከራከር ያስችላል፡፡ እዚህ ላይ መታሰብ ያለበት መሰረታዊ ሀሳብ የጀግና መቀነስ የጀግንነት ውርስና ትምህርትን በተያያዥነት የሚቀንስ መሆኑን ነው፡፡ በአድዋ ጦርነት የደረሰውን ጥፋት አማራ በራሱ ላይ አደረሰ ብሎ ለመናገር ከባድ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጅ አባቶቻችን አልተሳሳቱም ማለት አይቻልም፡፡ አሁን ላይ ተሁኖ ሲታሰብ ማድረግ የነበረባቸው ስልት ነበር፡፡ በእርግጥ ትናንትን በዛሬ መነጽር ማየት አይቻል ይሆናል፡፡ ሆኖም ወደኋላ መለስ ብሎ ማየቱ ለትምህርትነት ጥሩ ነው፡፡ እናም በአድዋ ጦርነት ጊዜ ሌላውን ብሔረሰብ ከፊት አስቀድመው እነሱ በአዋጊነትም በተዋጊነትም የመሳተፍን ዘዴ ተጠቅመው ቢሆን ኖሮ የሟች ጀግኖችን ቁጥር መቀነስ ይችሉ ነበር፡፡ እነሱ ግን እንደ ባህላቸው ቀድመው ደረታቸውን ለጦር ግንባራቸውን ለጦር አሳልፈው ሰጡ፡፡ ሌላውን ብሄረሰብ ከኋላ አስቀምጠው እነሱ ከፊት ተሰው፡፡ ያን ማድረጋቸው ባልከፋም ነበር፡፡ ነገር ግን እንደዛ ደጀን ሆነውለትና ሞተውለት ያተረፉት ብሄረሰብ ሁሉ ዛሬ እነዛን ሰማእታት አርበኞች ሲራገምና የእነሱን ልጆች እኛን ከማሳደድ አልፎ አርዶ እስከመብላት ሲደርስ ውለታ ቢስ ሲሆን ስናይ አሁን ከምንጽፈው በላይ ብናስብ የተገባ ነው፡፡ ምናልባት ያን ጊዜ ከፊት አሰልፈው አዋግተውት ቢሆን ኖሮ ብሔር ብሔረሰብ ሁሉ ጀግነትን፤ ታሪክን እና ለወገን መሞትን ይማር ነበር፡፡ ይህም ዛሬ በአርበኞቹ አጽምና ልጆች ላይ የሚያደርሰውን ግፍ ከማድረሱ በፊት የማሰብ አቅምና የማስታወስ እድል ይፈጥርለት ነበር፡፡ ባጭሩ እነሱን ከኋላ ጠብቆ ግንባር ሄዶ የሞተላቸው ብሔረሰቦች መልሰው ሲወጉት ስናይ ይህንን እናስባለን፡፡ በዚህም ሳቢያ ያ ጦርነት የትውልድ ስብራት ፈጥሮ በአማራ ላይ ጫና አሳድሮ አልፏል ብለን እንናገራለን፡፡ የማይጨው ጦርነት እና የአምስት አመቱ የአርበኝነት ትግል ከባድ ጉዳት አደርሷል፡፡ ጀግኖች ወደቁ፡፡ የጀግንነት ትምህርታቸውም አብሮ በየጢሻው ተቀበረ፡፡ የሚያሳዝነው በዛ ወቅት በተፈጠረ ስህተት አርበኞች ተገፍተው ወስላቶች እና አድር ባዮች ከጣልያን መውጣት በኋላ የመንግስትን ስልጣን ተቆጣጠሩ፡፡ በመንገስት መዋቅር ከላይ እስከታች ድረስ አርበኞች ገብተውበት ቢሆን ኖሮ ቀጣዩን ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሂደት መቀየር በቻሉ ነበር፡፡ ወይም ከዛ በኋላ አማራ ላይ የደረሱ ስብራቶች እንዳይከሰቱ የማድረግ አቅም ይኖራቸው ነበር፡፡ እውነተኛ ማህበረሰብ፤ ቆራጥ፤ ታማኝ እና ወገን ወዳድ የሆነ ትውልድ ቁጥሩ እንዲጨምር ማድረግ በቻሉ ነበር፡፡ የአርበኞች ተሰሚነት ማለት የአርበኛ ባህርያት ወደቀጣዩ ትውልድ የመተላለፍ እድላቸው ይሰፋ ነበር ማለት ነው፡፡ ያ ባለመሆኑ ግን በአብዛኛው የወስላታ ባህርይ እንዲተላለፍ ሆነ፡፡ እናም መጀመሪያ በማይጨው ጦርነት፤ ቀጥሎም በአርበኝነት የሞቱ አማሮች ትልቅ ክፍተት ፈጠሩ፡፡ ከዛ የተረፉትም አርበኞች በመገፋታቸው እና እንክብካቤ ያልተደረገላቸው በመሆኑ ሶስተኛው ዙር የትውልድ ክፍተት በአማራ ላይ ደረሰ፡፡ በእርግጥ ይህንን የአማራ ስህተት ብሎ ለመጥራት ይከብድ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጅ ፈጽሞ ነጻ ሊሆን አይችልም፡፡ ከጣልያን መውጣት

በኋላ ስልጣን ላይ የነበሩት አማሮች ነገሩን መስመር ማስያዝ ባለመቻላቸው እንደጥፋት ይቆጠራል፡፡ የ1953ቱ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ የተራረፉትን የአማራ ትላልቅ ሰዎች በሁለት ጎራ አሰልፎ አጫረሰ፡፡ ያን ጊዜ የደረሰው ውድቀት ተመልሶ ሊጠገን ባለመቻሉ መቆየት የቻለው 13 አመታትን ብቻ ነው፡፡ የ1953ቱ ጦስ የአማራን ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ህይወት እና እጣ ፋንታ በማመሰቃቀል ወደር አልተገኘለትም፡፡ አማሮች እርስ በእርስ በመተላለቃቸው የትውልድ ስብራት ተፈጠረ፡፡ የአማራው ትውልድም ቀጣይ እጣ ፋንታ በአስተማማኝ ድልድይ ላይ የመውደቁ ሁኔታ እየሳሳ መጣ፡፡ በእውነቱ ያ ጊዜ አሉ የተባሉትን ጀግኖች ያጣንበት ነው፡፡

የ1953ቱን መፈንቅለ መንግስት ያጀበው ወይም በብዛት የተከተለው የተማሪዎች እንቅስቃሴ አማራን በማዳከም ወደር አልተገኘለትም፡፡ የሌላውን ብሄረሰብ ልጅ ሁሉ በማስተባበር በራሳቸው አባቶች ላይ አዘመቱባቸው፡፡ የተፈጠረው ተከታታይ ግርግር ከ1953ቱ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ የተራረፉትን አማሮች ፋታ ነሳቸው፡፡ ለማንሰራራትም እድል ሳይሰጣቸው ቀረ፡፡ የመፈንቅለ መንግስቱ ጦስ ሲያንገዳግዳቸው የነበሩትን የተራረፉ አማሮች የተማሪ አመጽ ያዋከባቸው ነበር፡፡ በዚህ መሀልም በአሳቻ መንገድ የበታች መስመር መኮንኖች ስብስብ (ደርግ) እየተዋከቡ የነበሩ የተራረፉ አማሮችን ደፍቶ ጣላቸው፡፡ በዚህ በደርግ ውስጥም ወሳኝ የሆነ የአማሮች ቁጥር ነበር፡፡ ግን ሌላውን እንደራሳቸው በማመናቸው ውስጣቸው በተሰገሰጉ የሀማሴን፣ የትግሬና (በመጠኑም ኦሮሞነት ስሜት የነበራቸው) የበታች መኮንኖች ሰርጎ ገብነትና ተንኮል ሰለባ ሆኑና አካሄዳቸው ሁሉ ለአማራ ጦስ ሆነ፡፡ ከጣልን ጦርነት የተረፉ፣ ከ1953ቱ መከራ ያመለጡ የተራረፉ አማሮች በደርግ ግብአተ መሬታቸው ተፈጸመ፡፡ በመቀጠልም የመደብ ትግል በሚል ዘመቻ አማሮችን አስሮ፣ ገድሎ እና ሀብታቸውን ዘርፎ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አመናመናቸው፣ አዳከማቸው፡፡ በዚህም ውስጥ ፊውዳል እና አቆርቋዥ በሚል ሰበብ አማራን ትጥቁን በመግፈፍ ጀሌ አደረገው፡፡ ጀሌ እዲሆን በመደረጉም በኋላ የወያኔ ትግሬ እና የኦነግ የጥቃታ ሰለባ ሆነ፡፡ የትውልድ ስብራት ሙሉ በሙሉ ተከናወነ፡፡ በዛ ወቅት የመደብ ጠላት ማለት አማራ ማለት ነበር፡፡ ደርግ ውስጥ የነበረ አማራ በራሱ ስህተት እና በሌሎች ተንኮል በመደነባበር በራሱ ወገን ላይ ታሪክ ይቅር የማይለው በደል ፈጸመ፡፡ ከዛ ወዲህ የተከሰተው የአማራ ትውልድ የጀግና አባትን ምክርና ትምህርት ለማግኘት ያልታደለ ነበር፡፡ የት እንደሚሄድ እና ምን እንደሚያደርግም መንገዱ ሁሉ ተቀዠባበረበት፡፡ ግማሹ ኢህአፓ ሆኖ የሻእቢያና ጀብሀ መጫዎቻ ሆነ፡፡ ከፊሉ መኢሶን ሆኖ በኢትዮ-ኦሮሞ ፖለቲከኞች ሴራ ከኢህአፓ እና ደርግ ጋር ተጫረሰ፡፡ ኢህአፓም፣ ደርግም፣ መኢሶንም ሆኖ ቀይ እና ነጭ ሽብር አውጆ እርስ በእርሱ ተጨራረሰ፡፡ በእውነቱ ቀይ ሽብር እና ነጭ ሽብር የተፋፋመው በአማራ እና በአማራ ወጣቶች መካከል ነበር፡፡ ለአብነት በቀይ ሽብር ሰለባ አንደኛ ጎንደር ስትሆን ሁለተኛ አዲስ አበባ ነበረች፡፡ የጎጃም፣ የሸዋ (ከአዲስ አበባ ውጭ የነበረው) እና የላኮመልዛ አማራም ተመሳሳይ እጣ ነው የገጠመው--በሟች በቁጥር ብቻ ነበር ልዩነቱ፡፡ ከዛ ሁሉም በኋላ ለስም የተረፉት አማሮች በ1983ቱ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ሰበብ ተጨረሱ፡፡ ሲኒየር አማራ ብሎ ነገር እዚህ ጊዜ ላይ አበቃ (ከፕሮፌሰር አስራት ወልደየስና ጥቂት ጓደቻቸው በቀር)፡፡ እነሱ ላይ የደረሰውንም የምናስታውሰው ነው፡፡ ደርግ አማራውን ስላማረረውም ባለ አታሞዎቹን ወያኔ ትግሬዎችን ሰተት ብለው እንዲገቡ በር ከፈተላቸው፡፡ ደርግ ውስጥ በነበሩ አማሮች ተላላነት እና የተደገሰለትን ያላወቀው አማራ ደርግን በመዋጋት እና ወያኔን በመደበቅ አሳልፎ አዲስ አበባ አደረሰ፡፡

በኋላ ከንቱው አማራ የወያኔን መግባት ተከትሎ በአጃቢነት በትግሬና ኤርትራ የተዋቀረው ብአዴን አባል መሆን ጀመረ፡፡ ወያኔም እስካሁኗ ሰአት ድረስ ኢትዮጵያን በብአዴን ትከሻ ይዘውራታል፡፡ አማራን የሚያጠፋውም በዚህ ብአዴን ውስጥ በተሰባሰበ አማራ አማካኝነት ነው፡፡ ለወያኔ የኢትዮጵያ መግዣ አማርኛ ጽሁፍና ፕሮፓጋንዳ የሚቀመረው በዚህ

በብአዴንነት የተሰበሰበ አማራ ነው፡፡ አማራውን ቁርጡን አውቆ አምርሮ እንዳይታገል እግር ከወርች ያሰረው ይህ ብአዴን የተባለ የአማራ ስብስብ ነው፡፡ የነቁ አማሮችን እየመነጠረ ለወያኔ-ትግሬ የሚያስረክበውና የሚያሳርደውም ይህ ብአዴን ውስጥ የተሰበሰበ አማራ ነው፡፡ ታማኝነት በሚል ሰበብ በግብር መልክ አማራውን እያራቆተ ለትግሬ ጌቶች የአማራውን ሀብት የሚያስረክበው ብአዴን ውስጥ ያለው አማራ ነው፡፡ አማራው ላይ ከዘር ማጥፋት የማይተናነስ የወሊድ ቁጥጥር ሲደረግ ብአዴን ውስጥ ባለ አማራ ግዴለሽነትና ተባባሪነት ነው፡፡ በመድሀኒት እጥረት እና በስውር ደባ ህክምናዎች አማራው ላይ ለሚደርሰው በደል ሽፋን ሰጭው የብአዴን አማራ ነው፡፡ በአማራ መሀል ሰላምና ደህንነት ሳይኖር ሰላም ያለ የሚያስመልሰለው እና የሚያዘናጋው ይሄው ብአዴን ውስጥ ያለ አማራ ነው፡፡ የአማራን ጥንታዊና ክቡር ባህል ለመንከባከብና ከጥፋት ለመታደግ ምንም እንቅስቃሴ የማያደርገው ይህ ብአዴን ውስጥ ያለ አማራ ነው፡፡ የአማራ መሬት ትግራይ፤ ሱዳን እና ኦሮምያ ለተባሉ የጎረቤት አገራት እየተሸራረፈ ሲሰጥ ሽፋን ሰጭው እና ለምን ተብሎ ሲጠየቅም የሚያስተባብለው እና ጥንትም የእኛ መሬት አልነበረም የሚለው ይሄው ብአዴን ውስጥ ያለ አማራ ነው፡፡ ዛሬ ህዝቡ ከድህነት ብዛት የተነሳ ልብሱ ገላው ላይ አልቆበት ቅጠል ሰፍቶ ሊለብስ ትንሽ ቀርቶት ባለበት ሰአት አድገናል በልጽገናል እያለ የአማራውን ሰቆቃ በነጭ ፕሮፓጋንዳ የሚሸፍነው ይሄው ብአዴን ውስጥ ያለው አማራ ነው፡፡ አማራ ምድር ላይ የተመረተ የምድር ፍሬ አማራው ሳይቀምሰው ተጭኖ ትግራይን እና ሱዳንን ለመሳሰሉት የጎረቤት አገራት ሲጋዝ አጫጫኙ ይሄ ብአዴን ውስጥ ያለ አማራ ነው፡፡ የአማራው ቅርስ ተዘርፎና ተሸጦ ሲያልቅ አይኑን ጨፍኖ የሚያዘርፍ እና የሚያሻሽጥ ይህ ብአዴን ውስጥ ያለ አማራ ነው፡፡ ዛሬ በጉቦ በሚደረግ ልምድ አልባ ሾፌርነት ፈቃድ በየሰአቱ የአማራ ነፍስ በመኪና አደጋ እንደቅጠል እንዲረግፍ የሚያደርገው ይህ ብአዴን ነው፡፡ በጠቅላላው ይህ አድር ባይ እና አሳብጫ ቡድን ለአማራ መጥፋት ተወዳዳሪ የሌለው

አስታጽኦ እያደርገ ያለ ነው፡፡ በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ ከእጅ ወደአፍ በሆነ ክፍያ የሚያገለግለው የሲቪል ሰርቪስ አገልጋይ አማራም በአማራ መጥፋት ላይ እጁ አለበት፡፡ በእርግጥ ምርጫ የለውም፡፡ ምርጫም ባይኖረውም ጥፋቱን አለባብሶ ማለፍ አይቻልም፡፡ የወያኔ-ትግሬን አገዛዝ ካስማና ምሰሶ ሆኖ የያዘው ይህ የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ ይህ ክፍል የአገ›ሪቱ ቴክኖክራት ወይም ዘዋሪ ሀይል በመሆኑ የአማራ ደመኛ ጠላት የሆነው ወያኔ-ትግሬን ስልጣን በማራዘም እና ክንዱን በማፈርጠም ይህ ቀረሽ የማይባል አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ አማራ እንደብሔር የሚደቆሰው በዚህ ቴክኖክራት የአማራ ህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ ለራሱም እንዳይጠቀም ያገለገለውን ያህል እንዳያገኝ በሚያደርግ ስውር ማሰሪያ የተቀፈደደ ነው፡፡ ወገኑን ለመምቻነት መዶሻ ለመሆን ግን አማራጭ የሌለው ሀይል ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡ ለወያኔ ዋናው ጡንቻ የጦር ሰራዊቱ ሲሆን ዋናውን የቁጥርም ሆነ የጥራት ሚና እየተወጣ ያለው ራሱ አማራው ነው፡፡ ወያኔ-ትግሬ ዛሬ የሚዘባነነው የአማራን የጦር ሰራዊት ይዞ ነው፡፡ አማራን የሚሰድበውና የሚያንቋሽሸው እዲሁም ፈጽሞ ለማጥፋት የሚዝተውም ይህንን አማራዊ ክንድ ተማምኖ ነው፡፡ በጦር ሰራዊቱ ውስጥ ያለው አማራ በተለይ ለአማራ መጥፋት ግንባር ቀደም ተጠያቂ ነው፡፡ ምርጫ አጥቶ ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ግን ለወታደር ምርጫ አጥቶ የሚል ምክንያት መስጠት አይቻልም፡፡ ወታደር ምርጫን ይፈጥራል እንጅ ምርጫ አይሰጠውም፡፡ ምክንያቱም ለወታደር በአለቃውና በራሱ ነፍስ መካከል ያለችው ቀጭን ክር የራሱ ጥይት እርሳስ ናት፡፡ ያም ባይሆን ወታደር ነውና የራሱን አማራዊ ምርጫ መፍጠር ይገባዋል፤ ይጠበቅበታልም፡፡ በአንድነት ስም የሚወዛገበው አማራ ለአማራ መጥፋት የራሱን አስተዋጽኦ ሲያደርግ የቆየ እና እያደረገ ያለ ነው፡፡ አማራው በራሱ ተሰባስቦ የራሱን እጣ በእጁ እንዳያስገባ መሰናክል እየሆነ ያለው ይህ የአንድነት አዚም የተጠናወተው አማራ ነው፡፡ በእርግጥ ወደወገኖቹ ቢዞር እና የአማራነትን እቅስቃሴ ቢቀላቀል ፈጣን እና ጥልቅ ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው ይህ በአንድነት ጎራ ውስጥ ያለው አማራ ነው፡፡ አቅሙ እና ተነሳሽነቱ ከፍተኛ በመሆኑ ወደአማራዊ ትግል ቢቀየር የአማራን ሰቆቃ ማሳጠር የሚችል ሀይል ነው፡፡ ነገር ግን አማራው እንዳይደራጅ ትልቁ እቅፋት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህ ሀይል ምኞታዊ እንጅ ተግባራዊ እውነታዎችን ለመገንዘብ አልቻለም፡፡ የአንድነቱ ነገር

ከተጨባጭ እውነትነት ርቆ ምኞታዊ ብቻ መሆኑን ባለመገንዘቡ በማይገባ ቦታ ጉልበት፤ ገንዘብና እውቀቱን እያጠፋ ይገኛል፡፡ የዚህ ሀይል መኖር የአማራን ብሄረተኝነት ስሜት በታሰበው ፍጥነትና ስፋት እንዳይራመድ አድርጎታል፡፡ የአማራ ብሄረተኝነት መጎልበት እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ ምስራቅ አፍሪካ ውስጥ ለምናያቸው ችግሮች ፍቱን መድህኒት መሆኑን መገንዘብ ባለመቻሉ ደንቃራ ሆኖአል፡፡ በጠቅላላው አማራው ላይ ለደረሰው ጥፋት እና ለሚደርሰው ጥፋት የአማራው ድርሻ የማይናቅ ነው፡፡ መፍትሄውም መላው የአማራ ልጅ አሰላለፉን ማስተካከል ነው፡፡ ይህ ሁሉ በስሁታን መስመሮች ተሰልፎ የሚገኝ አማራ መስመሩን አስተካክሎ አማራዊ ሰልፍ ያደረገ እለት የአማራ ሰቆቃ ያልቃል፡፡ ድል ለአማራ! አማራነት ወደፊት!

መለከ ሐራ ከቤተ

አማራ